# ለረጅም ጊዜ አገልግሎቶችና ድጋፎች (LTSS) በቨርጂኒያ Medicaid የሚሰጥ የጤና ሽፋን

## እርስዎ ወይም የሚያውቁት ሰው ከሚከተሉት መካከል በሁለቱ ወይም ከዚያ በላዩ ላይ እገዛ ማግኘት ትፈልጋላችሁ?



አመጋገብ ገላ መታጠብ አለባበስ



ማዛወር የሽንት ቤት አጠቃቀም መራመድ

## ከሆነ የሚከተሉት መውሰድ ያሉብዎ እርምጃዎች ናቸው:

- የተግባር መስፈርትን ያሟሉ እንደሆነ (ከላይ በተመለከቱት የእለታዊ አኗኗር ስራዎች ላይ እገዛ ያስፈልግዎት እንደሆነ)፣ የህክምና/የነርስ እንክብካቤ ፍላጎት እንዳልዎት እና በ30 ቀናት ውስጥ የነርስ እንክብካቤ ተቋም ምደባ የመፈለግ ስጋት ውስጥ ስለመሆንዎ ለመወሰን ይመርመሩ።
    - ማጣሪያው/ ምርመራው በሚከተሉት ቦታዎች የሚገኙ የህክምና ሙያተኞችን በሚይዝ ቡድን ይካሄዳል:
        - ሆስፒታሎች፣
        - የማህበረሰብ አገልግሎቶች ቦርዶች፣
        - የጤና መምሪያዎች እና የማህበራዊ አገልግሎቶች ድርጅቶች።
- ለMedicaid LTSS አገልግሎቶች ያመልክቱ ይህን በሚከተለው መልኩ ማድረግ ይችላሉ:
    - በስልክ ቁጥር 1-855-242-8282 (TDD: 1-888-221-1590) ይደውሉ።
    - በኦንላይን በ www.commonhelp.virginia.gov፣ ወይም
    - በአካባቢ የማህበራዊ አገልግሎቶች ኤጀንሲ መምሪያ (በመልእክት ወይም ማመልከቻውን በአካል በማስገባት)።
- የገንዘብ ማስተላለፊያ መረጃ በመስጠት –የLTSS ክፍያ ግለሰቡ የንግድ ወይም የግል ንብረቱን ካስተላለፈና ለዚህም በቂ ክፍያ ካልተቀበለ ሊከለከል ወይም ለብዙ ወራት ሊዘገይ ይችላል።
- የገቢ መረጃ በመስጠት – የገቢ ጣሪያ አለ። በተጨማሪም ግለሰቦች በገቢ መጠን ላይ ተመስርቶ የእንክብካቤውን ወጪ (የታካሚ የክፍያ ኃላፊነት) መክፈል ሊኖርባቸው ይችላል።
- የገቢ ምንጭ መረጃ በማቅረብ – የገቢ ምንጭ ከተቀመጠው ገደብ በላይ ከሆነ ግለሰቡ ብቁ አይሆንም።

| በተቋም ለሚደገፉ ግለሰቦች የገቢና የገቢ ምንጭ ጣሪያዎች * | | |
|---|---|---|
| **የቤተሰብ መጠን** | **የገቢ ጣሪያ** | **የሀብት ገደብ** |
| 1 | $2,829 | $2,000 |

**አገልግሎቶች**

የረጅም ጊዜ አገልግሎቶችና ድጋፎች ስር የሰደደ ህመም ወይም አካል ጉዳት ያለባቸው እና ያለ እገዛ ለረጅም ጊዜ እራሳቸውን መንከባከብ የማይችሉ ሰዎችን የህክምናና የህክምና ያልሆኑ ፍላጎቶቻቸውን እንዲያሟሉ ለመርዳት የሚቀርቡ አገልግሎቶች ናቸው።

አገልግሎቶቹ የሚፈቀዱ ከሆነ በነርስ እንክብካቤ አገልግሎት መስጫ፣ በቤት ውስጥ ወይም በማህበረሰብ መቼት ሊቀርቡ ይችላሉ።

* *ገቢ ከስራ የሚገኝ ገንዘብን፣ የማህበራዊ ዋስትና ገቢ ን፣ የዘማቾች ጥቅማ ጥቅሞችን፣ ጡረታዎችን ወይም የውርስ ገቢዎችን ያጠቃልላል። የገቢ ምንጮች የቼክ/ቁጠባ ሂሳቦች፣ ስቶኮች፣ ቦንዶች፣ የህይወት መድን ዋስትና ወይም የጡረታ ፈንዶች የመሳሰሉ ነገሮች ናቸው።*

**በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች መልሶችን ጨምሮ ስለ ሽፋን የተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት www.coverva.orgን ይጎብኙ ወይም ለማመልከት በስልክ ቁጥር 1-855-242-8282 ይደውሉ።**

VIRGINIA'S MEDICAID PROGRAM DMAS

Revised: 08/19/2024